[Subject:] በበላይ ተቆጣጣሪው የተጻፈ መልእክት

ማርች 23ቀን 2020ዓ.ም.

የFCPS ቤተሰቦች እንደምን ዋላችሁ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት አገረ ገዢው Northam በቨርጂንያ ከK-12 ያሉት ት/ቤቶች ለቀሪው የትምህርት ዘመን እንደሚዘጉ አስታውቀዋል፡፡ ይህ በጣም ተስፋ አስቆራጭ ዜና ነው ። ነገር ግን የቫይረሱ ስርጭት ለመግታት ሁላችንም የበኩላችንን ለማድረግ እየጣርን ያለንበትን ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ለመረዳት የሚቻል ውሳኔ ነው፡፡

የትምህርት ቤታችን ቦርድ ዛሬ ከሰዓት በኋላ የአስቸኳይ ጊዜ ስብሰባ እየተሰበሰበ ነው ፡፡ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ፈታኝ ሁኔታ ቢገጥመንም የሚቀጥለውን እርምጃ ለመወሰን ከእነሱ ጋር በቅርበት እሠራለሁ፡፡

በሚያሳዝን ሁኔታ በአገረ ገዢው ማሳሰቢያ መሰረት በተጨማሪ የስርአተ ትምህርቶች መርሃግብሮች ፣ የአካል እንቅስቃሴ መሃግብሮች እና የማህበረሰብ መጠቀሚያ አገልግሎቶች እስከ ቀሪው የትምህርት ዓመት ሁሉም ተሰርዟል፡፡

ምንም እንኳን ት/ቤቶች ዝግ ቢሆኑም ግባችን ለተማሪዎቻችን ቀጣይነት ያለው ትምህርት መስጠታችንን መቀጠል ነው። የVirginia Department of Education (VDOE) ለትምህርት ቤት ወረዳዎች ፍትሃዊነት ላይ ያተኮረ ትምህርት መስጠት እንዲቀጥሉ በሚቀጥሉት ቀናት ተጨማሪ መመሪያ ይሰጣል። በተጨማሪም VDOE ለ12ኛ ክፍል ተመራቂዎች ምን ዓይነት የምረቃ መስፈርቶች እንደሚኖር እና ለሁሉም ተማሪዎች የደረጃ ማውጣት እና የቀለም የትምህርት ዓመት ማጠናቀቂያ  መመሪያ ይሰጣል ፡፡

ወደ እማናውቀው መንገድ እየተጓዝን ነ ፣ ሆኖም እያንዳንዱ ሰው ፈተናውን ለማሸነፍ እየተነሳ በመሆኑ እኮራለሁ። ጥንቃቄ ያድርጉ እና ደህንነትዎን ይጠብቁ። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ አብረን እንደምንጸና አውቃለሁ ፡፡

ከልብ:-

Scott. Brabrand, Ed.D

Fairfax County የህዝብ ትምህርት ቤት